# «እልል በሉ!»

## «ኦባማ ነኝ» የሚል ወንድ በመብራት ሃይል አዳራሽ ተወልዷል

**አቤ ቶኪቻው**

abeto2007@yahoo.com

የዛሬ ወሬያችን አቦል ሜክሲኮ መብራት ሃይል አዳራሽ ውስጥ በረካ ከስቴድየም ወደ ሽሮሜዳ በሚወስድ ታክሲ ውስጥ እንዲሁም ቶናውን ምናለሽተራ ላይ እናፈላዋለን ይበሉ ወዳጄ ጨስ ጨስ እያደረጉ ይከተሉኝ፡፡

ታዲያ ለቡና ቁርስ ይሆነን ዘንድ ሰላምታ ይዝገኑልኝ፡፡ እንዴት ሰነበቱ ወዳጄ ቀዬው አማን ውሎም አላደረም? ዘመድ አዝማድ ቤተሰብ ባጠቃላይ ግራ ቀኙ በጎ ሰንብቷል? ጎሽ  ሰላምዎ ሰላሜ ነውና ሁሌም ሰላም ይሁኑልኝ ወዳጄ!

**<u>አቦል</u>፡-**

ቅዳሜ እግሬ ወደ ሜክሲኮ መርቶኝ ነበር፡፡ እንደምን? ማለት የጨዋታ ደንብ ነውና እንደምን ይበሉኝ፡፡ ይሔውልዎ በሳምንቱ መጀመሪያ አካባቢ በሆነ ጋዜጣ ላይ **ደመቅ** ብሎ የተፃፈ ማስታወቂያ ተመለከትኩኝ፡፡ «ለምክንያታዊ ፖለቲካ ደጋፊዎች በሙሉ!» ይላል፡፡ ማስታወቂያውን እንደ እኔ በእርጋታ ያላነበቡ ሰዎች በንባብ ግድፈት ይሁን አሽሙር መናገር ፈልገው ይሁን በይገባኝም «ለምክኒያታዊ...» የሚለውን «ለመካኒቷ ፖለቲካ ደጋፊዎች...» ብለው አንብበውታል፡፡ ስብሰባው የተጠራው በጋዜጣ ማስታወቂያ ብቻ ሳይሆን በመኪና ላይ «ሀሎ ሀሎ» ጭምር ነበር፡፡ ታድያ የማጀቢያው ዘፈን አፈሩን ገለባ ያድርግለትና የጋሽ ጥላሁን «ኡኡ ብዬ አለፍኩ ሁሉን ችዬ» የሚለው ዘፈን ነበርና ይህንን የሰማ አንድ ወዳጄ «ሁሉን የቻልነውስ እኛ» አለኝ፡፡ «አናንተ ደግሞ ስንተኛው አማራጭ ናችሁ?» ስለው «የማንም መቀለጃ የሆንኩኝ ህዝብ ነኝ እንጂ፡፡» ብሎኝ ነበር፡፡ ለማንኛውም ስብሰባውን የጠራው «ኢዴፓ» ፓርቲ ነው፡፡

«ፓርቲው እና አመራሮቹ ከዘጠና ሰባት ምርጫ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ከህዝብ ጋር ለመገናኘት ጥሪ ያደረጉት፡፡» የሚለውን ነገር ስሰማ «እስከዛሬ  ከህዝብ ጋር ለመገናኘት ምን ቸገራቸው? ናፍቆቱስ እንዴት አስቻላቸው?» ብዬ አንድ ወዳጄን ብጠይቀው «እስከዛሬማ  ከህዝብ ጋር ሳይሆን ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር እየተገናኙ በርካታ ጉዳዮችን ሲደግፉ ስራ በዝቶባቸው ነበር የከረሙት፡፡» አለኝ፡፡ እንዲህ ሲለኝ በእውነት ሆዴ ተንቦጫቦጨ፡፡ አራት አመት ሙሉ የደገፉበት ክንዳቸው አልዛለም ይሆን? የሆነ ሆኖ «ኢዴፓ» ፓርቲ ከአራት አመት በኋላ

የመጀመሪያውን ህዝባዊ ስብሰባ ጠራ:: እናም ገሚሱ የመካኒቱ (ይቅርታ የምክኒያታዊ ማለቴ ነው) ፓለቲካን ደግፎ፣ ገሚሱ ደግሞ «ሔጄ ልክ ልካቸውን ልንገራቸው» ብሎ እንደ እኔ አይነቱ ደግሞ የስብሰባው ሶስተኛ አማራጭ ሆኖ ሁላችንም በአዳራሹ ታድመናል:: በነገራችን ላይ «ኤዴፓ ሶስተኛ አማራጭ ፓርቲ ነው::» የሚል ነገር በሰማሁኝ ጊዜ አንድ ወዳጄን «ይህ ማለት ምን ማለት ነው» ስል ጠይቄው ነበር:: ወዳጄ እንደማንኛውም የተማረ ሰው ንግግሩን «ዌል...» በምትለው እንግሊዘኛ ቃል አጅቦ አብራራልኝ «አየህ ኢዴፓ ሶስተኛ አማራጭ ነው ሲባል ከአጋር ትንሽ ከፍ ከ(ኢህአዴግ)አባልነት ደግሞ ትንሽ ዝቅ ብሎ የሚገኝ ማለት ነው» ብሎኛል:: ታድያ እኔም «ከምክኒያታዊ ፖለቲካ ደጋፊዎች» ዝቅ «ከልክ ልክ ነጋሪዎች» (እነዚህ ሰዎች አሉባልተኛ እንደሚባሉ በኋላ ላይ ገለፃ ተደርጓል::) ብቻ ከእነርሱ ደግሞ ከፍ ብዬ ሶስተኛ አማራጭ ተሰብሳቢ በመሆን የታደምኩት ለዚህ ነው::

በቅድሚያ የፓርቲው ሊቀ መንበር አቶ ልደቱ ስለ ፓርቲቸው አንዳንድ ነጥቦችን አነሱ:: ንግግራቸውን በጥሞና እየተከታተልኩኝ ሳለ በመሃል እርሳቸው እና ፓርቲያቸው ማለት ኦባማና ዴሞክራቲክ ፓርቲ ማለት መሆኑን አበሰሩን:: ምንም እንካዕ አንዳንዶች «ኦባማ አንደዋዛ!» ሲሉ ቢያሽሚጥጧቸውም እኔ ግን ከዚህ በፊት አንድ ጋዜጣ ላይ የሰጡትን ቃለ ምልልስ እያስታወስኩኝ ነበር::አቶ ልደቱ «ሰዎች ከማንዴላ ጋር ያመሳስሉኝ ነበር በድጋሚም ከይሁዳ ጋር አመሳሰሉኝ እኔ ግን ሁለቱንም አይደለሁም::» ብለው ነበር:: ታድያ እኒህ ሰው ማናቸው? ብለን ስንጨነቅ ለካስ ሰውየው ኦባማ ነበሩና:: አቶ ልደቱ «እኔ ማለት ኦባማ ማለት ነኝ» ብለው ብቻ አላበቁም «ኦባማን በዚህ አዳራሽ ስታገኙት እልል አትሉምን?» ሲሉ በትዝብት ጠየቁ በጉድ የወጣሁ! ርስት አድርገነው!! «እልልልል....» ወዳጄ እልልታው ቀለጠልዎታ!

በርግጥ አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች እኒህ ሰው በ«አረም...» መፀሃፋቸው ውስጥ «ቆራርጠን እንጥልሃለን ይሉኛል እውን ኢትዮጵያ ከዚህ በኋላ ወንድ ታበቅል ይሆን?» ሲሉ ጠይቀው ነበር:: ይኸው «ኦባማ ነኝ» የሚል ወንድ በመብራት ሀይል አዳራሽ በቀለላት:: እልልታ ያንሳል ሲሉ አሽሚጠዋል::

እዚህ ጋር አንድ ዘግይቶ ወሬ ያቀበለኝ ወዳጄ አቶ ልደቱ ህዝብ «ማንዴላ» ያላቸው ጊዜ ስቅስቅ ብለው አልቅሰው እንደነበረ ቢያወጋኝ ምንይሁን ብለው ነበር ያለቀሱት? አልኩት «ያን ጊዜ ሰውየው እንደዛሬ ግብዝ አልነበሩምና (ነጠላ ሰረዝ) ያንጊዜ ሰውየው ሁለት ነብስ ኖሮ ሁለቱ በሞትኩላችሁ ይሉ ነበርና(ቃል አጋኖ) ማንዴላ ሲባሉ አለቀሱ (ትምህርተ ስላቅ)::» አለኝ:: «አልገባኝም::» አልኩት ወዳጄን በሰጨት ብሎ «አትመኑኝ እኔ ማንዴላ ሳልሆን ይሔ አዲስ የመጣው የኮምፒውተር ቫይረስ (ዱላ) ነኝ ማለታቸው ነው::) ሲለኝ «ውይ ውይ ተው ጡር አትናገር::» ብዬ ስመክረው ስመክረው ዋልኩኝ እልዎታለሁኝ::

ከዛማ ስብሰባውም እየደራ እየደራ መጣልዎ:: እኔ የምለው አንዳንዱ ሰው እንዴት እንዴት ነው የሚናገረው እባክዎ? አንዱ አስተያየት ሰጪ ምን እንዳሉ ያውቃሉ? «ኦባማውን» ሰውዬ «እናውቅሃለን የስልጣን ጥመኛ ነህ እውነቱን ነገሩኝ ካልክ የኢህአዴግ አጋር ነህ!!» አላሉትም መሰልዎ? እስቲ በሞቴ «ሰለማዊ ትግልን የላቀ ደረጃ እንዲደርስ የማይናቅ አስተዋፅኦ» ያደረጉ የተከበሩ ሰው እንዲህ ማለት ይገባል? (አፈር ስሆን ወዳጄ የተከበሩ ስል ትዝ ያለኝን ፖለቲካ አልባ ጨዋታ በቅንፍ እንዳወጋዎ ይፍቀዱልኝ:: ይሔውልዎ አንድ ወዳጅ አለኝ:: ይኽ ወዳጄ እንደ አወላለዱ «አንቱ» የሚባል እንደ ዖታው ደግሞ አንተ የሚባል የተከበረ ሰው ነበር:: ታድያ ምን ይሆናል ሰዉ በመንገድ፣ በስራ ቦታ፣ እንዲሁም በጨዋታ ቤት የሰውነት አቋሙን እየገመገሙ አንተንም ትተው አንቱንም ትተው «አንቺ» እያሉ ቢጠሩት ጊዜ ነገሩ ትክን አያደርገው መሰልዎ? ታድያልዎ ይኼ ወዳጄ ልጆቹን ከጓደኞቻቸው ጋር ቀላቅሎ ፎቶ አስነሳልዎታ ከዛማ «አንቺ» ሲሉት «እንከባበር ብቀጥንም ወላድ ነኝ» እያለ አንድ መዋለ ህፃናት ሙሉ ፎቶ ያሳይዎታል:: ችግሩ የተከበሩ ያስብለኛል ብሎ የዘየደው ዘዴ ወዳጃችንን ለሌላ ትችት መዳረጉ ነው:: ከተቺዎች አንዱ በሽልማት መልክ ምን እንደሰጠው ያውቃሉ? «የወሊድ ቁጥጥር ዘዴዎች እና ጥቅማ ጥቅሞቹ» የሚል ትልቅ መፀሃፍ:: ወዳጄ ቅንፉ ሞቀኝ መሰል ብዙ ቆየሁበት በሉ ከቅንፍ ውጪ ይከተሉኝ) እናልዎ አንዳንዶች የተከበሩትን ሰው «የተቀበሩ» ብለው ለመጥራት ሲቃጣቸው ብስጭት ብዬ «አቶ ልደቱ የተከበሩ ሰው ስለመሆናቸው የግድ የፓርላማ መታወቂያቸውን ማሳየት የለባቸውም::» ስል ተናገርኩልዎታ ልክ አላልኩም? ስብሰበው ደራ ብዬዎትም አልነበር? ታድያልዎ ሰብሳቢው ከአንድ ደቂቃ በላይ አልሰጥም ብሎ እነርሱ በፓርላማው አፈ ጉባኤ ደረሰብን ሲሉት የነበረውን ጫና (ወይስ ይሔ ነገር ኢዴፓ ላይ አልደረሰም?) ብቻ ጠያቂዎች በአንድ ደቂቃ ጥያቄያችሁን ጨርሱ ሲባልልዎ አንዱ አስተያየት ሰጪ «ችግራችሁ ብዙ ደቂቃችሁ ትንሽ ስለሆነ ጥያቄዬን በምህፃረ ቃል አቀርባለሁኝ ብሎ ያሰናዳውን አይቼ ስቄ ስቄ ላባራልዎ ነው?

ወዳጄ በአጠቃላይ ኢዴፓ ባለፉት አራት አመታት «በአሉባልታ ቸነፈር ሲገረፍ እና በስራይ ቤት ወሬ ሲታመስ» የከረመውን ያህል ዛሬ ለዚች ቀን በመብቃቱ በርካቶች እንደ ልደት ቀናችን እናከብረታለን ሲሉ ማዳመጤን አልሸሽግዎትም::

አቦሉ ይሻልዎታል ብዬ አበዛሁብዎ መሰለኝ በሉ ወደ በረካው እንደሚከተለው እንሒድ:: በረካችን በመጨረሻም ብለን እንጥራው::

*በመጨረሻም 1 ከስቴድየም ወደ ሽሮሜዳ በሚወስድ ታክሲ ውስጥ ተሳፍሬያለሁኝ:: ከአጠገቤ (አንዳንድ አሉባልተኞች እንደሚሉት) ወዝሩን እንደ ፖለቲካ ምህዳሩ ያጠበበች አንድ ባለ ሰፊ ዳሌ ኮረዳ ተቀምጣለች:: ከኮረዳይቱ ጋር አንዳንድ ሃገራዊ ጨዋታዎችን እየተጫወትን እና ልማታዊ ውይይቶችን እያወራሁዋት ጉዞአችንን*

*ቀጠልን:: ልጅት ስለ ሃገር ኢኮኖሚ እድገትም፣ስለ ገበያ መር ግብርናም ስለ ምንም ግንዛቤ የላትም (ወይም አውቃ ለግማለች) «ቆይ አንቺ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ አስራ አንድ ነጥብ ሁለት በመቶ እንደሚያድግ እምነት የለሽም?» ስል ጠየኳ፬ት:: ልጅት አልገባትም መሰል ፈገግ አለች:: ታክሲው ዳገቱን ሲያያዘው «አየሽ ቁጥር የሚከብድሽ ከሆነ የሃገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት እንደዚህ ዳገት ይመሰላል::» ብላት ሙሉ የታክሲው ሰው ሳቀ:: ሳቁ የደስታ ይሁን የፌዝ አልገባኝም:: አሁንም ምህዳሩ በተጣበበው ወንበር ላይ እንደምንም እየተመቻቸሁኝ «አየሽ ለመንግስታችን ብቻ እድሜ ለምኚ እንጂ አስራ አንድ በመቶ ብቻ ሳይሆን መቶ አንድ በመቶ እናድጋለን» አልኳ፬ት:: ልጅት ለመንግስታችን እድሜ ለምኚ ያልኳ፬ት ጊዜ «ቤተመንግስት ወራጅ አለ!» አለች:: «ምን ለማለት ፈልገሽ ነው? የምን ወራጅ?» የሚሉ ጥያቄዎቼን እንዳልሰማ ዝም ብላኝ ወረደች:: አትሳሳቺ እህቴ ቤተ መንግስት ጋ ወራጅ የለም! አልኩኝ ጮህ ብዬ::*

*በመጨረሻም 2 (ቶና) ወዳጄ ሰሞኑን ምናለሽ ተራ የስራ ጉዳይ ሲያመላልሰኝ ከርሟል አንዳንዶች (ምን ልትሸጥ?) ሊሉ ቢችሉም ምናለሽ ተራ ግን ምን አለሽ? የሚባልባት ብቻ ሳትሆን ምን ትፈልጊያለሽ? የሚባልባትም ነች:: እውነት እውነት እላችኋለሁኝ ምናለሽ ተራ ፈልጋችሁ ያጣችሁት ነገር ካለ አልተፈጠረም ማለት ነው:: በዛ ላይ የአካባቢው ሰዎች የማይሰሩት አይነት ስራ የለም:: አሮጌ ወደ አዲስ እንዴት እንደሚቀየር ለማየት ከፈለጉ መሄድ ያለብዎ ምናለሽ ተራ ነው:: አንዳንዶች ሲናገሩ እንደሰማሁት ከሆነ መንግስት ስራ ፍጠሩ ብሎ ከማወጁ በፊት ምናለሽ ተራዎች በፈጠራ ተጠምደው የከረሙ ሰዎች ናቸው ታድያ በፈጠራ ወሬ ሳይሆን በፈጠራ ስራ ነው:: ምናለሽ ተራ ወሬ ቦታ የለውም ስራ ብቻ!! እንዴት ያስደስታል? ረዥም እድሜ ለምናለሽ ተራ!*

*ወዳጄ አቦሉንም በረካውንም ቶናውንም ተቃምሰናል:: ሰላም ለዛሬ ይብቃና?!*
*አማን ያሰንብተን ወዳጄ!?*